ቁጥር 10 ግንቦት 2015 10ኛ ዕትም በነፃ የሚታደል

ኮሙኒኬሽን ቢሮ
Communication Bureau

# አዲስ ዜና

ቁጥር 10 ግንቦት በአዲስ አበባ ኮሙኒኬሽን ቢሮ በነፃ የሚታደል

**ሰው ተኮር የልማት ስራዎች በከፊል**

**በከተማ አስተዳደሩ እየተገነቡ ያሉ ሜጋ ፕሮጀክቶች**

**የበጎ ፍቃደኞች የእውቅና መርሀ ግብር**



**እርስ በራሳችን ብንተባበር እና ብንሰራ ብዙ በጎነት እና የዜጎችን እንባ የማበስ ተግባር መስራት እንችላለን!**

# የአዲስ አበባ ኮሙኒኬሽን ቢሮ

**የተቋሙ ራዕይ /Vision/**

በ2022 ዓ.ም ጠንካራ የኮሚዩኒኬሽን ስርዓት በመዘርጋት በቂና የተሟላ መረጃ ያለው፤ በከተማዋ ሁለንተናዊ እድገት ንቁ ተሳትፎ የሚያደርግ ህብረተሰብ በመፍጠር ከተማችን አዲስ አበባን የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት ሆና ማየት፡፡

**የተቋሙ ተልዕኮ**

በቢሮው የተለያዩ የኮሙኒኬሽን አግባቦችን በመጠቀም ዘመናዊ ፣ግልጽ እና ፈጣን ምላሽ መስጠትን ባህሉ ያደረገ የኮሙኒኬሽን ስርዓት በመዘርጋትና በዘርፉ መሪ ሚና በመጫወት ብሎም በመንግስትና በህዝብ መካከል ጥራት ያለውና እና ለሁሉም ነዋሪ ተደራሽ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር በማድረግ፦

## የተቋሙን እሴቶች /Values/

- ተጠያቂነት፤
- ብዝሃነት፤
- ግልፅነት፤
- ተአማኒነት፤
- የጋራ መግባባት መፍጠር፤
- ለጊዜ የላቀ ዋጋ መስጠት፤
- ለገጽታ ግንባታ ስኬት ግንባር ቀደም ሚና መጫወት፤

**በአዲስ አበባ ከተማ ኮሙኒኬሽን ቢሮ**

**የህዝብና ሚዲያ ግኑኙነትና ይዘት ዘርፍ የሚዘጋጅ ወርሃዊ ዜና መጽሔት**

**ስልክ**

**ኢሜል**

**ዌብ ሳይት**

# በሰው ተኮር የልማት መርሃ ግብር የተገነቡ ቤቶችን ለአቅመ ደካሞች እና ለልማት ተነሺዎች ተላለፉ





የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በ90 ቀናት የሰው ተኮር የልማት መርሃ ግብር የተገነቡ ቤቶችን ለአቅመ ደካሞች እና ለልማት ተነሺዎች አስተላልፈዋል።

ቤቶቹ ከተላለፈላቸው መካከል በከተማው እየተከናወነ በሚገኘው የወንዝ ዳርቻ ልማት ከጉለሌ እና አራዳ ክፍለ ከተሞች የተነሱ ነዋሪዎች ይገኙባቸዋል።

እርስ በራሳችን ብንተባበር እና ብንሰራ ብዙ በጎነት እና የዜጎችን እንባ የማበስ ተግባር መስራት እንችላለን ብለዋል ከንቲባ አዳነች አቤቤ ፤በቤቶቹ ግንባታ ሂደት ድጋፍ ላደረጉ አካላትም ምስጋና አቅርበዋል።

ለወገኖቻችን ቤት መስጠት ብቻ ሳይሆን ያለን ሀብት በፍትሃዊነት የማዳረስ ሀላፊነታችንን የመወጣት ተግባርን ጭምር ነው ያከናወነው ሲሉም ከንቲባዋ ገልፀዋል።

የወገኖቻችንን ችግር ስንጋራ ፍቅርን እየሰጠናቸው ከጎናቸው መሆናችንንም እየገለጽንላቸው መሆኑን መረዳት ይገባል ብለዋል ከንቲባዋ።

የከተማ አስተዳደሩ የነዋሪውን የቤት ችግር ለመፍታት እየሰራ መሆኑን ያስታወቁት ከንቲዋ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ዜጎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ባለሀብቶችን በማስተባበር የሚስሩ ቤቶች 20ሺ መድረሳቸውን ተናግረዋል።

በመሃል ከተማ በተለይም በወንዝ ዳርቻ ልማት ሳቢያ ለሚነሱ ነዋሪዎች የከተማ አስተዳደሩ ትናንት ሲኖሩበት ከነበረው እጅግ በተሻለ የመኖሪያ አካባቢ እንዲኖሩ እያደረገ እንደሚገኝ የተናገሩት ከንቲባ አዳነች ዜጎቻችን የአደጋ ስጋት ካለባቸው አካባቢዎች ወደ ተሻለ ኑሮ እያሸጋገርን እንገኛለንም ብለዋል።

# ከተማ አስተዳደሩ ለበጎ ፍቃደኞች እውቅና ሰጠ





ከንቲባ አዳነች አቤቤ በ2014 በጀት ዓመት የተሰሩ የበጎ ፍቃድ ስራዎች እንዲከናወኑ ድጋፍ ላደረጉትና ላስተባበሩ አካላት ምስጋና አቅርበዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር "በጎ ፈቃደኝነት ለዘላቂ አብሮነት" በሚል የ 2015 የበጎ ፈቃድ የእውቅና እና የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ማስጀመሪያ መርሀግብር የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በተገኙበት ተካሂዷል፡፧

በመርሀግብሩ ላይ ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ፣የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ብዙ ትርጉም አለው ያሉ ሲሆን የበርካታ የከተማዋ ነዋሪዎችን ህይወት መቀየሩን ተናግረዋል፡፡

እንዲሁም በጎ ፍቃድ አገልግሎት ፍትሃዊ የሀብት ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ በማድረግ በኩል ትልቅ ሚና እንዳለው ጠቁመዋል፡፡

የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ዜጎችን ማፍቀርና ማክበርን በተግባር እንድናሳይ አስችሎናልም ነው ያሉት ከንቲባዋ፡፡

በጎነት በከተማዋ ባህል እንዲሆን ፣በጎ ማገልገል የከተማዋ መገለጫ እንዲሆን ማስመስከር እንደተቻለም አንስተዋል፡፡

ባደጉ ሀገራት ዜጎች በበጎ መስጠት እንዲታወቁ ለማድረግ የህግም የፖሊሲም አቅጣጫ መኖሩን ያነሱት ከንቲባዋ ማህበራዊ ሃላፊነትን መወጣት እኛም ሀገር ህግ መሆን አለበት ብለዋል፡፡

## በክረምት በጎ ፈቃድ ስራ የ3 ሺህ 500 መኖሪያ ቤቶችን ዕድሳት ተጀመረ


ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከሶስት ቀናት በፊት ያስጀመሩትን የክረምት በጎ ፈቃድ ስራ ተከትሎ በከተማ ደረጃ 3 ሺህ 500 የሚሆኑ የመኖሪያ ቤት ዕድሳት ማስጀመራቸውን የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ አስታወቁ።

ባለሀብቶችንና ሕዝቡን በማስተባበር የበርካታ ነዋሪዎችን ችግር መቅረፍ የሚያስችል የቤት እድሳት መርሀ-ግብር በልደታ ክፍለ ከተማ በተለምዶ ቆርቆሮ ሰፈር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ተጀምሯል።

መርሀግብሩ ከ18 ዓመታት በላይ በቆርቆሮ ቤት ውስጥ የሚኖሩ 134 አባወራዎችን እና በአራዳ ክፍለ ከተማ ራስ መኮንን ድልድይ አካባቢ የሚኖሩ 15 አባወራዎችን መኖሪያ ቤት ዕድሳት በማስጀምር መጀመሩን ከንቲባዋ አስታውቀዋል፡፡

ከንቲባዋ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት፣"የከተማችንን ገጽታ የሚቀይር ታላላቅ ፕሮጀክቶችን ከመገንባት ጎን ለጎን በሰው ተኮር ስራዎቻችን የሀገር ባለውለታዎችንና አቅመ ደካማ ነዋሪዎችን ከከተማዋ ዕድገት ፍትሐዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በትጋት መስራታችንን እንቀጥላለን" ሲሉም ገልጸዋል::





# ‹‹በጎ ፈቃደኝነት ለዘላቂ አብሮነት››በሚል መሪ ሀሳብ የ2015 ዓ.ም የክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መርሃ ግብርን አስጀምሯል





የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2015 ዓ.ም የበጎ ፈቃድ የእውቅና፣የምስጋናና የክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መክፈቻ መርሃ ግብር አካሂዷል።

በመርሃ ግብሩ ላይ ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ አገልግሎት ማስተባበሪያ ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ አብርሃም ታደሰ ባለፉት ወራት በበጎ ፈቃድ አገልግሎት የተከናወኑ ተግባራትንና በቀጣይ ክረምት ሊከናወኑ የታቀዱ ተግባራትን አብራርተዋል፡፡

ከግንቦት 2015 ዓ.ም እስከ መስከረም 2016 ዓ.ም ድረስ በሚቆየው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መርሃ ግብር ሊሰሩ ከታቀዱ ተግባራት መካከል ደግሞ፡-

2 ሚሊየን በጎ ፈቃደኞች በተለያዩ የበጎ ፈቃድ አግልግሎት ዘርፎች ይሳተፋሉ፡፡

3 ነጥብ 5 ቢሊየን ብር የሚገመት ሀብት ይሰበሰባል፣በዚህም 1 ነጥብ 2 ሚሊየን የመዲናችን ነዋሪዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

በማዕድ ማጋራት መርሃ ግብር 1 ቤተሰብ ለ1 ህፃን መርሃ ግብር ይካሄዳል

ስጦታየ ለአዲስ አበባየ በሚለው መርሃ ግብር በሰብአዊ አገልግሎት 1 መቶ ህፃናትን በጉዲፍቻና በስፖንሰር ለማሳደግ ድጋፍ የሚደረግበት ይሆናል፡፡

3ሺ500 ቤቶች በማህበራዊ አገልግሎት ይታደሳሉ፡፡

በትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ደግሞ 30 ሺ ወጣቶች ከአባቶቻቸውና የተሻለ አቅምና እውቀት ካላቸው ግለሰቦች የስብዕና ግንባታ ይሰጣቸዋል፡፡

50ሺ ተማሪዎች የማጠናከሪያ ትምህርት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

በአይሲ ቲና በሌሎች ዘርፎች አጫጭር ስልጠናዎች ይሰጣሉ፡፡

በአካባቢ ጥበቃና በአረንጓዴ ፕሮግራሞች ከ15 ሚሊየን በላይ ችግኞች ይተካላሉ ብለዋል አቶ አብርሃም፡፡

በሌሎች ዘርፎችም ማለትም በከተማ ግብርና ፣በጤናና ቀይ መስቀል፣በኤች አይ ቪ ምርመራና ግንዛቤ ማስጨበጥ ፣በመንገድ ትራፊክ፣በአካባቢ ሰላም ማስጠበቅና እሴት ግንባታ፣በኪነ ጥበብና መዝናኛ፣በስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች፣በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣በወሰን የለሽ የበጎ ፈቃድ አገልግሎትና በማህበራዊ ሚዲያ ፕሮግራሞች በርካታ ስራዎችን ለመስራት ታቅዶ ወደ ተግባር መገባቱን ነው አቶ አብርሃም ያብራሩት፡፡

# አዲስ አፍሪካ አለም አቀፍ ኮንቬንሽንና ኤግዚቢሽን ማዕከል ግንባታ አፈፃፀም 76 ከመቶ መድረሱ ተገለጸ



የአዲስ አፍሪካ አለም አቀፍ ኮንቬንሽንና ኤግዚቢሽን ማዕከል ግንባታ አፈፃፀም 76 ከመቶ መድረሱን የአዲስ አበባ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽ/ቤት አስታወቀ፡፡

አጠቃላይ የፕሮጀክት ስራውን በአንድ መቶ አስር ሺ ካሬ ሜትር መሬት ላይ ለማሳረፍ በሶስት የግንባታ ምዕራፍ እቅድ ተይዞ እየተሰራ ከሚገኘው ከዚህ ግዙፍ ፕሮጀክት ግንባታ መካከል የምዕራፍ አንድ ግንባታ ስራ በመፋጠን ላይ እንደሚገኝ የጽህፈት ቤቱ መረጃ ያሳያል፡፡

በአዲስ አበባ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽ/ቤት የአዲስ አፍሪካ አለም አቀፍ ኮንቬንሽንና ኤግዚቢሽን ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክት ክትትልና ድጋፍ ሰጪ ባለሙያ የሆኑት ታደለ ዳንደና (ኢ/ር ) እንደገለፁት በከተማ አስተዳደሩ ልዩ ትኩረት የተሰጠው እና ከፍተኛ የኢኮኖሚ ምንጭ ይሆናል ተብሎ የሚጠበቀው ይህ ግዙፍ ፕሮጀክት በፍጥነት ተጠናቆ ለአገልግሎት እንዲበቃ ጽህፈት ቤቱ ተገቢ የሆነ የቴክኒክ ድጋፍና ክትትል ሥራ እያደረገ ይገኛል ብለዋል፡፡

የፕሮጀክት ግንባታው ክትትል ስራ አስኪያጅ ጌትነት በሻህ (ኢ/ር) በበኩላቸው አዲስ አበባን የምስራቅ አፍሪካ የግብይት ማዕከል ለማድረግ እየተሰራ የሚገኘው ይህ ትልቅ የግንባታ ፕሮጀክት ከአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ጀምሮ በከተማው አስተዳደር ሜጋ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽ/ቤት እና ሌሎች አካላት ብርቱ የድጋፍና ክትትል ስራ አማካኝነት የፕሮጀክቱ ግንባታ አፈፃፀም 76 ከመቶ መድረሱን ተናግረዋል፡፡

ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅም በከተማዋ ሁሉን አቀፍ ገፅታ ላይ የጎላ አስተዋጽኦ ከማድረጉ ባሻገር በተለያየ የሙያ መስክ ላይ ለሚገኙ ዜጎች በቋሚና ጊዚያዊነት ሰፊ የስራ እድል ይፈጠራል ተብሎ ይጠበቃል፡፡



# ቆሼ አካባቢ የአደጋ ስጋት ተጋላጭ የሆኑ ነዋሪዎችን ከቦታው የማንሳት ስራ በአጭር ቀናት ውስጥ እንደሚጠናቀቅ ተገለፀ





በተለምዶ ቆሼ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የአደጋ ስጋት ተጋላጭ የሆኑ ነዋሪዎችን ከቦታው የማንሳት ስራ በአጭር ቀናት ውስጥ እንደሚጠናቀቅ በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የአዲስ አበባ ስራ አስኪያጅ አቶ ጥራቱ በየነ ተናገሩ።

ስራ አስኪያጁ የአደጋ ስጋት የሆነውን የደረቅ ቆሻሻ ማከማቻ ቦታ አካባቢ የሚኖሩ ነዋሪዎችን የማንሳት ሂደቱ ያለበትን ደረጃ ከሌሎች የካቢኔ አባላት ጋር በመሆን ጎብኝተዋል።

የደረቅ ቆሻሻ የሚከማችበት ቆሼ ከዚህ በፊት ተደርምሶ በሰውና በንብረት ላይ ጉዳት ማስከተሉ ይታወሳል።አደጋው ከተከሰተ ጀምሮም የአካባቢውን ነዋሪዎች ከቦታው የማንሳት ስራ ሲሰራ መቆየቱ ይታወሳል።

ከዚህ ቀደም የተነሱ ነዋሪዎችም ምትክ እንዲሰጣቸው ካሳ እንዲከፈላቸው የማድረግ ስራ ሲሰራ መቆየቱን አካባቢውን የጎበኙት የከተማዋ ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ጥራቱ በየነ ተናግረዋል።

ከዚህ ቀደም አጣዳፊ የአደጋ ስጋት ያለባቸው ነዋሪዎች መነሳታቸውን ያወሱት አቶ ጥራቱ ቀሪ 25 ነዋሪዎችም ተገቢው ካሳና ምትክ ቦታ ተዘጋጂቶላቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ ይነሳሉ ብለዋል።

በአካባቢው በህገ ወጥ መንገድ ላስቲክ ወጥረው የሚኖሩ ከ300 በላይ ነዋሪዎችም አስቸጋሪ የአደጋ ስጋት ያለባቸው በመሆኑ በፍጥነት ከስጋት ነጻ እንዲሆኑ የማድረግ ስራም በትኩረት ይሰራል ነው ያሉት አቶ ጥራቱ።

በወንዝ ዳርቻዎችና እንደዚህ አይነት የአደጋ ስጋት ያለባቸው ቦታዎች ላይ የሚኖሩ ነዋሪዎች የአደጋ ተጋላጭነትን ለመቀነስ የሚሰራውን ስራ በመደገፍ ሊተባበሩ እንደሚገባም ጥሪ ቀርቧል።

የቆሼ ደረቅ ቆሻሻ ማከማቻ ቦታ በየቀኑ ከተማዋ የምታመነጨውን ከ2ሺ.400 እስከ 2ሺ.800 ቶን የሚደርስ ቆሻሻ ይከማችበታል።

# በትምህርት ቤቶች አቅራቢያ በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳዳሩ 2 ሺህ 662 የንግድ ቤቶች ላይ ርምጃ መወሰዱ ተገለፀ






በትምህርት ቤቶች አቅራቢያ ተማሪዎችን ታሳቢ አድርገው የተቋቋሙና በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳዳሩ 2 ሺህ 662 የተለያዩ የንግድ ቤቶች ላይ ርምጃ መወሰዱ ተገለፀ።

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ጋር በመተባበር ያዘጋጀው በትምህርት ቤቶች አካባቢ የሚገኙ የተለያዩ የንግድ ተቋማትና መጠጥ ቤቶች በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የሚያስከትሉትን ተፅዕኖ የሚዳስስና ችግሩን መከላከል በሚቻልባቸው መንገዶች ላይ የሚመክር የውይይት መድረክ እየተካሄደ ነው።

የሚገኙ የመጠጥ ፣ የሺሻ እና የጫት ቤቶች በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የሚያስከትሉት ተፅዕኖ ትውልድ ላይ የተጋረጠ ፈተና መሆኑን ተናግረዋል።

ይሄንን ትውልድ ላይ የተጋረጠ ፈተና በመከላከል መልካም ስብዕና ያላቸው ዜጎችን ለመፍጠርም አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በተለያዩ የሚዲያ አማራጮችና ቋንቋዎች በችግሩ መንስኤና መፍትሔ ላይ ትኩረት ያደረጉ ዜና እና ዘጋቢ ፊልሞችን እየሰራ መሆኑን አንስተዋል።

በትምህርት ቤቶች አካባቢ የሚስተዋሉ አዋኪ ተግባራትን በመከላከል አገር ተረካቢ ትውልድ ለማፍራት የተቋማት ቅንጅት አስፈላጊ መሆኑን ደግሞ የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ሃላፊ ዘላለም ሙላቱ (ዶ/ር) ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለስልጣን ም/ስራ አስኪያጅ አቶ ደሳለኝ ፉፋ በበኩላቸው፣ ባለፉት ዘጠኝ ወራት በትምህርት ቤቶች አቅራቢያ ተማሪዎችን ታሳቢ አድርገው በተቋቋሙና በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ባሳዳሩ 2 ሺህ 662 የተለያዩ የንግድ ቤቶች ላይ ርምጃ መወሰዱን አስታውቀዋል።

## በአዲስ አበባ የሚተከሉ 800 ሺህ የሚደርሱ ችግኞች ተዘጋጅተዋል



ለዘንድሮው አረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በአዲስ አበባ በተለያዩ ተቋማት የሚተከሉ 800 ሺህ የሚደርሱ ችግኞችን ማዘጋጀቱን የጉለሌ እጽዋት ማዕከል ገለጸ።

የጉለሌ ዕጽዋት ማዕከል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ጉተማ ሞረዳ እንደገለጹት በዘንድሮው ዓመት በአዲስ አበባ በተለያዩ ተቋማት የሚተከሉ 800 ሺህ ችግኞች ተዘጋጅተዋል።

በዚህም ችግኝ ለሚያፈሉና ለሚያቀርቡ ዜጎች የሥራ እድል በመፍጠር ወጣቶቹ ገቢያቸውን ማሳድጉን ነው የገለጹት።

ማዕከሉ ለዘንድሮው ዓመት የአረንጓዴ አሻራ መርሃ-ግብር አገር በቀል የሆኑ ለአፈርና የውሃ ጥበቃ፣ ለፍራፍሬና ለምግብነት የሚውሉ ጨምሮ አካባቢን ለማስዋብ የሚውሉ ችግኞችን አፍልቶ ማዘጋጀቱን ጠቁመዋል።

በአገር አቀፍ ደረጃ ባለፉት አራት ዓመታት በተካሄደው የአረንጓዴ አሻራ መርኃ ግብር 25 ቢሊየን ችግኞች መተከላቸው ይታወሳል።

## በመዲናዋ ከ300 ሺህ በላይ ዜጎች በከተማ ግብርና ስራ በመሰማራት ውጤታማ ስራ እያከናወኑ ነው





በመዲናዋ ከ300 ሺ በላይ ዜጎች በከተማ ግብርና ስራ በመሰማራት ውጤታማ ስራ እያከናወኑ መሆኑን በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የአዲስ አበባ ከተማ ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ጥራቱ በየነ ገለጹ፡፡

አቶ ጥራቱ “ከቤተ ሙከራ ወደ አዝመራ” በሚል መሪ ሃሳብ በሳይንስ ሙዚየም የተዘጋጀውን የግብርና እና የሳይንስ አውደ ርዕይን ጎብኝተዋል፡፡

“ምግቤን በጓሮዬ” እና አንድም መሬት ጾም ማደር የለበትም በሚል መሪ ሃሳብ የተጀመረው የከተማ ግብርና ስራ ውጤት ማምጣቱንም ነው የተናገሩት፡፡

በከተማዋ ከ300 ሺህ በላይ ዜጎች በከተማ ግብርና ስራ በመሰማራት ውጤት እያመጡ መሆኑን በመግለጽ ህብረተሰቡ ባለው ክፍት ቦታ ላይ የከተማ ግብርና ስራን በማከናወን ኑሮ ውድነቱን ማረጋጋት ይቻላል ብለዋል ፡፡

በከተማ የሚስተዋለውን ስራ እጥነት ቁጥር ለመቀነስ ወጣቱ ስራን ሳይንቅ በከተማ ግብርና ስራ ተሰማርቶ ውጤታማ እንዲሆንም አቶ ጥራቱ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

## የሠላም ሠራዊት አባላት የከተማዋን ሠላምና ጸጥታ ዘላቂና አስተማማኝ እንዲሆን በማስቻል በኩል የማይተካ ሚና መጫወታቸው ተገለጸ

የሠላም ሠራዊቱ አባላት የከተማዋን ሠላምና ጸጥታ ዘላቂና አስተማማኝ እንዲሆን በማስቻል በኩል የማይተካ ሚና መጫወታቸውን የአዲስ አበባ ሰላም እና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ሠላምና ጸጥታ አስተዳደር ቢሮ በከተማዋ ከሚገኙ ከ1000 በላይ የሠላም ሠራዊት አባላት ጋር የ9 ወራት የስራ አፈጻጸሙ ላይ ውይይት ተካሂዷል።

በመድረኩ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከሁለት ሺህ በላይ የወንጀል ድርጊቶችን በማጋለጥ ተጠርጣሪዎች ለፍትህ እንዲቀርቡ በማድረግ ረገድም የሠላም ሠራዊቱ የላቀ ሚና ነበረው ተብሏል።

ከ1500 በላይ ሕገወጥ የጦር መሣሪያ በቁጥጥር ስር መዋሉም ተመላክቷል።

የሠላም ሠራዊቱ አባላት የከተማዋ ሠላምና ጸጥታ ዘላቂና አስተማማኝ እንዲሆን በማስቻል በኩል የማይተካ ሚና መጫወታቸውንም ቢሮው አስታውቋል።





# 6ኛ ዙር የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ስራ ተጀመረ





በአዲስ አበባ ከተማ በ6ኛ ዙር በተመረጡ በሰባት ክፍለ ከተሞች ከግንቦት 03/09/2015 ዓ.ም ጀምሮ ባሉ ተከታታይ አምስት ወራት 50 ሺህ የመሬት ይዞታዎችን የማረጋገጥ ስራ እንደሚካሄድ የአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አስታውቋል፡፡

የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ ግፌወሰን ዴዲሳ እንደገለጹት፡- ምዝገባው በኮልፌ ቀራኒዮ፣ በቂርቆስ፣ በንፋስ ስልክ ላፍቶ፣በቦሌ፣በአዲስ ከተማ፣ በልደታና በአራዳ ክፍለ ከተሞች ባሉ 50 ቀጠናዎችና 211 ሰፈሮች ይከናወናል ብለዋል።

ይህ የይዞታ ማረጋገጥ እወጃ ከተላለፈ ከ15 ቀናት በኃላ የይዞታ ይረጋገጥልኝ ጥያቄዎች በክፍለ ከተማ ቅ/ጽ/ቤቶች ቀርበው ጥያቄዎቻቸውን ማቅረብ የሚችሉ መሆኑን አቶ ግፋወሰን ዴዲሳ ተናግረዋል፡፡

ለመሬት ይዞታ ማረጋገጥ በተመረጡ ቀጠናዎችና ሰፈሮች ስራው ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ባለቱ አምስት ወራት ውስጥ የመረጃ ልዩነት እንዳይፈጠር ሲባል ምንም ዓይነት የስመ- ንብረት ዝውውር አገልግሎት እንደማይሰጥም የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ ግፌወሰን ዴዲሳ አስታውቀዋል፡፡

ኤጀንሲው በአዋጅ ከተቋቋመ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በ5 ዙር 147 ሺህ ይዞታዎችን በካዳስተር ሲስተም መመዝገቡ አስታውቋል፡፡

## የሆቴል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ዓለም አቀፍ ፕሮቶኮልን ጠብቀው እንዲሰሩ ተጠየቀ፡፡



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል ፣ኪነጥበባት እና ቱሪዝም ቢሮ ከደንብ ማስከበር ባለስልጣን ጋር በመተባበር የሆቴል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከአዋኪ ድርጊቶች፣ ልዩ ልዩ የወንጀል ተግባራት ፣ የአገሪቱን ባህሎች ጠብቆ መስራትን ጨምሮ በዘርፉ ያሉ ዓለም አቀፍ ፕሮቶኮሎችን አክብረው አገልግሎት መስጠት በሚችሉበት አግባብ ላይ ያተኮረ ውይይት ተደርጓል ።

በውይይቱ መክፍቻ ላይ የአዲሰ አበባ ባህል ኪነጥበባትና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶ/ር ሂሩት ካሳው ተቋማት ለአገር ውስጥና ለውጭ እንግዶቻቸው ዓለም አቀፍዊ የዘርፉን ፕሮቶኮሎች የሚያሟላና የአገሪቱን ገጽታየሚያስጠብቅና ተቀባይነት ያለው አገልግሎት መስጠት እንደዳለባቸው ገልፀዋል።

# በቀን 288 ሺህ እንጀራ የሚጋገርበት ማዕከል ተመረ



በአዲስ አበባ ከተማ በቀን 288 ሺህ እንጀራ የሚጋገርበትና እንጀራን ኢንዱስትራላይዝ በማድረግ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የሆነው ለሚ እንጀራ ማዕከል ተመረቀ፡፡

ማዕከሉ ከ2 ሺህ እናቶች በተጨማሪ በተለያዩ የስራ መስኮች ለ1ሺህ ነዋሪዎች በአጠቃላይ ለ3 ሺህ ወገኖች የስራ ዕድል እንደሚፈጥር ተገልጿል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ከተለያዩ ከተሞች ከንቲባዎች ጋር በመሆን ማዕከሉን መርቀዋል፡፡

ለሚ እንጀራ ማዕከል የእናቶችን ድካም የሚያቀልና እንጀራን ከፍ ባለ ደረጃ ማምረት የሚያስችል መሆኑን ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገልጸዋል፡፡

ማዕከሉ ከፈተናዎቻችን በላይ ሆነን የማይቻል የሚመስለውን የመቻላችን ማሳያ ነው ብለዋ ከንቲባዋ፡፡

በየቦታው ያለንን አቅም፣ ገንዘብ እና እውቀት በማስተባበር የነዋሪዎችን ሸክም የሚያቀሉ ፕሮጀክቶችን በመንደፍ እየተገበርን ሲሉ አመላክተዋል፡፡

ኦቪድ ግሩፕ 170 ሚሊየን፣ ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ 75 ሚሊየን፣ መድህን ድርጅት 20 ሚሊየን ብር፣ መታሰቢያ ታደሰ ኮንስትራክሽን 500 ዘመናዊ ምጣዶችን በማቅረብ እንዲሁም የታተ ምግቦች ደግሞ በማማከር ለማዕከሉ ዕውን መሆን ላበረከቱት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከንቲባ አዳነች በእናቶች ስም አመስግነዋል፡፡






## ህብረተሰቡን የከተማው ሰላምና ፀጥታን የማስከበር እንቅስቃሴ ባለቤትነትና ማዕከል ማድረግ ያስፈልጋል ተባለ ፡፡





የአዲስ አበባ ሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ከተጠሪው የደንብ ማስከበር ባለስልጣን ጋር ዘላቂ ሰላምና ፀጥታን ጨምሮ ልዩ ልዩ የደንብ ጥሰቶችን ለመከላከል የተወሰዱ እርምጃዎችን ጨምሮ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ጥቅል አፈጻጸም ተገምግሞ ቀጣይ የሥራ አቅጣጫ ተቀምጧል።

በግምገማ መድረኩም አዋኪ ድርጊቶችን፣ የሽብር መልክ ያላቸው የሰርጎ ገቦች የጥፋት እንቅስቃሴ፣ ከኢ-መደበኛ የንግድ እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ የፀጥታና የትራፊክ እንቅስቃሴ መስተጓጎሎችን፣ የተደራጀ ሌብነትን ፣ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር፣ የመሬት ወረራን ጨምሮ ህገ ወጥ ግንባታን ለመከላከል የተወሰዱ እርምጃዎች በጥልቀት ተገምግመዋል ።

የሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ ወ/ሮ ሊዲያ ግርማ ለበርካታ የፀጥታ እክሎች ተመጣጣኝ መፍትሔ በመስጠት ከተማዋን የልማትና የዲፕሎማሲ ማዕከል እንድትሆን ለማስቻል ህብረተሰቡን በማስተባበርና የሰላሙ ባለቤት በማድረግ እየተሰራ ነው ብለዋል።

ህብረተሰቡ ከጸጥታ ተቋማት ጋር አበረታች የፀጥታ ተግባራትን ማከናወን መቻሉን የጠቀሱት የቢሮ ኃላፊዋ ይህም ቅንጅታዊ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ መቀጠል ይገባዋል ብለዋል።

ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ በበኩላቸው ከህብረተሰቡ ጋር በመቀናጀት ልዩ ልዩ የደንብ ጥሰቶችን የመከታተል ፣መቆጣጠርና እርምጃ መውሰድን ጨምሮ የመሬት ወረራን በዘላቂነት ለመግታት የሚያስችሉ ቅንጅታዊ እርምጃዎች የተወሰዱ መሆናቸውን አረጋግጠዋል ።

ተሳታፊዎችም በበኩላቸው ህዝቡን የከተማው ሰላምና ፀጥታ እንቅስቃሴ ማዕከልና ባለቤት በማድረግ ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ መስራት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

---

## በመዲናዋ የጤናውን ዘርፍ አገልግሎትን ለማሻሻል በተከናወኑ ተግባራት ውጤት ተመዝግቧል





የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ በስሩ በሚገኙ ሆስፒታሎች እና ጤና ጣቢያዎች ከተወጣጡ የጤና ባለሙያዎች ጋር ውይይት አድርጓል፡፡

የከተማ አስተዳደሩ ባለፉት 5 አመታት የጤናውን ዘርፍ አገልግሎትን ለማሻሻል አዳዲስ ሆስፒታሎች እና ጤና ጣቢያዎች እንዲሁም የህብረተሰብ ጤና አገልግሎት መስጫ መሰረተ ልማቶች መገንባታቸውን የጤና ቢሮ ኃላፊ ዶ/ር ዮሃንስ ጫላ ተናግረዋል::

ወረቀት አልባ አገልግሎትን በሁሉም የጤና ተቋማት በማስፋት ቴክኖሎጅ ተኮር የጤና አገልግሎት ስርዓትን በዘላቂነት ለመገንባት ርብርብ እየተደረገ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

በ10 ወረዳዎች ተገድቦ የነበረው የጤና መድን አሁን በሁሉም ወረዳዎች ተደራሽ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በዚህም ከሁለት ሚሊዮን በላይ ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን የቢሮ ሀላፊው ገልፀዋል።

የጤናውን አገልግሎንት በሚፈለገው ደረጃ ለማሳደግ ቅንጅታዊ አሰራሮችን ይበልጥ ማሳደግ ይገባል ተብሏል፡፡

የጤና ባለሙያዎችን ለማበረታታት ከግብር ነፃ ማድረግን ጨምሮ ሌሎች መሰል እርምጃዎችን እንዲወስድ ጠይቀዋል፡፡